የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.67
ADDIS ABABA 21st July, 2020

**ማውጫ**

## Content

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፰/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……………ገጽ ፲፪ሺ፮፻፹፱

Proclamation No.1218/2020

Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda Ratification Proclamation........................Page 12,689

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፰/፪ሺ፲፪

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በኪጋሊ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱን ማፅደቅ በወንጀል ምርመራና ክስ እና የወንጀል ፍሬን ከማገድና መውረስ አኳያ የሚደረግ በወንጀል ጉዳዮች ዓለም አቀፍ ትብብርን የሚያበረታታ እና የሚያጠናክር በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባው ያፀደቀው በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO. 1218/2020

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE MUTUAL LEGAL ASSISTANCE IN CRIMINAL MATTERS AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF RWANDA

WHEREAS, the Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda has been signed in Kigali, on the 28th day of April, 2017;

WHEREAS, ratifying the Agreement promotes and strengthens international cooperation in criminal matters for the investigation and prosecution of offences and freezing and confiscation of the proceeds of crime;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 25th day of June, 2020;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፰/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሩዋንዳ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል ሚያዝያ ፳ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም. በኪጋሊ የተፈረመው በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የፍትሕ ትብብር ስምምነት ፀድቋል፡፡

## ፫. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን የማስፈፀም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda Ratification Proclamation No.1218/2020".

## 2. Ratification of the Agreement

The Mutual Legal Assistance in Criminal Matters Agreement signed in Kiglai on the 28th day of April, 2017, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Rwanda is hereby ratified.

## 3. Responsibility of the Attorney General

The Attorney General of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby authorized to follow up the implementation of the Agreement in collaboration with other government organs.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on publication in the *Federal Negarit Gazette*.

**Done at Addis Ababa, on this 21st day of July, /2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**